## ምድብ አራት (ከ7ኛ - 9ኛ ክፍል)

## 22 ኛ ሳምንት

# የሰሎሞን ጥበብ

**ዓላማ**

- ለማጥናትም ይሁን ማንኛውንም በጎ ነገር ከመሥራት በፊት በምድር ላይ የእግዚአብሔር ጥበብ እንደሚያስፈልገን ማስገንዘብ::

**ጥቅስ**

- «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው::» መዝሙር 110 ÷ 10

**ምንባብ**

- 1ኛ ነገሥት 3 ÷ 16-27

**መግቢያ**

- ያለፈውን ጊዜ ትምህርትና ጥቅስ ጥያቄ–ችን በመጠየቅ ያስታውሷቸው::
- ለትምህርቱ መርጃ የሚሆን ሥዕል ያዘጋጁ::

**የትምህርቱ መግለጫ**

- ሰሎሞን የሚባል ታላቅ ንጉሥ ነበር::
- ሰሎሞን ከአባቱ ከዳዊት ቀጥሎ ንጉሥ ሆነ::
- በሥራው ሁሉ ሞገስን እነዲሰጠው በእግዚአብሔር ፊት ሊጸልይ ወደ ገባዖን ሄደ::
- እግዚአብሔር ተገልጦ ምን እንድሰጥህ ትፈልጋለህ? ብሎ ጠየቀው::
- ሰሎሞንም ሀብት፣ የጠላቶቹን ሞት ፣ ረጅም ዕድሜንም አልለመነም::
- ነገር ግን ጥበብ ስጠኝ ብሎ ጠየቀ::
- እግዚአብሔር ደስ ተሰኝቶ ሁሉንም ሰጠው::
- በጥበቡም ሕዝቡን ማስተዳደር ጀመረ::
- ሕዝቡም ሁሉ ተገንዝበው እግዚአብሔርን አመሰገኑ::
- አንድ ቀን ሁለት ሴቶች ይፈርድላቸው ዘንድ በንጉሡ ፊት ቆሙ::
- ሁለቱን ሴቶች ታማኝዋ ሴትና ያልታመነችዋ ሴት ብላችሁ ጥሩአቸው::
- ሁለቱም ያለቅሱ ነበር::
- ሁለቱም ይካሰሱ ነበር::
- ሁለቱም ሴቶች በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ነበሩ::
- ሁለቱም ሴቶች ወንዶች ልጆችን ወለዱ::
- በአንድ ሌሊትም ያልታመነችዋ ሴት በልጅዋ ላይ ተኛችበት ታፍኖም ሞተ::
- በሌሊትም ተነስታ የሞተ ልጅዋን ወስዳ በአጠገብዋ በነበረችው የታመነችዋ ሴት ደህና ልጅ ለወጠችው::
- የታመነችው ሴትም በጠዋት ተነስታ ልታጠባው ስትል ልጁ ሞቷል:: አዘነች አለቀሰችም::
- በአትኩሮትም ተመለከተችውና ልጅዋ እንዳልሆነ አወቀች::
- ወዳልታመነችውም ሴት ሄዳ የሞተው ልጅ ያንቺ ነው የኔ ልጅ የት አለ? ብላ ጠየቀቻት:: ያልታመነችውም የሞተው ያንቺ ነው ብላ ካደቻት::
- የእውነተኛ እናት ስሜት ምን እንደሚመስል ልጆች እንዲገጹ ያድርጓቸው::
- በመጨረሻም ይፈርድላቸው ዘንድ ወደ ንጉስ ሰሎሞን ሄዱ::
- በነጋታው በቤተ መንግስትም የነበሩ ሰዎችም ሁሉ በመገረም ሁኔታውን ይመለከቱ እና ይሰሙ ነበር::
- ችግሩ እንዴት ይፈታል? ንጉሡ ምን ያደርጋል? ደህነኛው ልጅ ከሁለቱ የየትኛይቱ ሴት እንደሆነ ይረጋገጣል? ሁለቱም ያለቅሱ ነበር:: ሁለቱም አዝነው ነበር:: ልጆች ይወያዩበት::
- ንጉሥ ሰሎሞንም በእግዚአብሔር ፊት ቆም የሚፈርድበት ጥበብን ይሰጠው ዘንድ ጸለየ::
- ከጸለየም በኋላ ሰይፍን ያመጡለት ዘንድ አገልጋዮቹን አዘዛቸው:: ሰይፉንም አመጡለት::
- ንጉሡም «ደህነኛውን ሕፃን ለሁለት ቆርጣችሁ ግማሽ ግማሽ አከፋፈሉአቸው::» አለ::
- ታማኟና እውነተኛይቱ ሴት አንጀትዋ ስለልጅዋ አዝኖና ራርቶም «ጌታዬ ሆይ ልጁን ለእርስዋ ስጣት እንጂ አትግደለው::» አለች::
- ያልታመነችውና የሞተ ልጅዋንም በሌሊት በመቀየር ለማታለል የፈለገችው ሴት ግን ንጉሡን «ልጁ ሁለት ቦታ ይከፈል እንጂ ለእኔም ለእርሷዋም አይሁን::» አለች::
- ንጉሡ ሰሎሞንም «ልጁ አይገደል ያለችው ሴት እናቱ ናትና ደህነኛውን ሕፃን ለእርስዋ ስጡአት አትግደሉት::» አለ::
- የእስራኤልም ሰዎች ሁሉ የፈረደውን ፍርድ በሰሙ ጊዜ ንጉሡን ፈጽመው አከበሩት:: ምክንያቱም እግዚአብሔር የተስተካከለ ፍርድን ይፈርድ ዘንድ ጥበብን እንደሰጠው አውቀዋልና::
- ሕዝቡም «እግዚአብሔር ጥበብን ለሚለምነው ሁሉ ይሰጣል:: የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው::» አሉ::
- ችግሩ ምን ያህል ከባድና አዲስ እንደነበረ ተወያዩ::
- ሕፃኑን ሁለት ቦታ የመቁረጥም ፍርድ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ጥበብ እንደነበረ ልጆች ይወያዩበት::

**ማጠቃለያ**

- የሰሎሞን ልመና ምን ያህል የተወደደ ነበር!!! ሀብትን አልለመነም፤ የጠላቶቹንም መሞት አልለመነም:: ነገር ግን ጥበብ እንዲሰጠው ብቻ ለመነው :: ልጆች የናንተ ልመና እና ፍላጎት ምን እንደሆነ እስኪ መዝኑ:: መንፈሳዊ ነው ወይስ እነደሰውነታችሁ ፈቃድ ብቻ የሆነ ነው?
- ጥበብ ለመንፈሳዊ የሕይወት ጉዞም ሆነ ለዕለት ከዕለት ሕይወታችን አስፈላጊ ነው::
- የብርሃናት አምላክ እግዚአብሔር ጥበብን ይሰጣችሁ ዘንድ ወደርሱ ጸልዩ::

**ተግባር**

- ከጥናታችሁና ለፈተናም ከመቀመጣችሁ በፊት እግዚአብሔር ጥበብን ይስጣችሁ ዘንድ ጠይቁት ጸልዩም::
- የሚከተሉትን ክፍት ቦታዎች ሙሉ::
    1. ንጉሥ ሰሎሞን እግዚአብሔር --------------- ይሰጠው ዘንድ ለመነ:: እግዚአብሔርም ሰጠው::
    2. ንጉሥ ሰሎሞን ሕፃኑ ------------------ ሴት እንጂ ----------------- ሴት አይደለም አለ::
    3. ንጉሥ ሰሎሞን የንጉሥ ----------------- ልጅ ነበር::

**ይቆየን::**